# በወንዞቻችን የውሃ መበከልን ለመቀነስ፣ ለዝናብ በርሜል ተመላሽ ማግኘት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

በዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ወደ ወንዞቻችን የሚገባውን የተበከለ ውሃ እንዲቀንስ አስተዋጽኦ ለማድረግ በመኖሪያ ህንጻዎች፣ በንግድ ህንጻዎች እና በማህበረሰብ ቦታዎች ላይ የዝናብ በርሜሎችን ቢያስቀምጡ፣ ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ። የዝናብ በርሜሎች ከጣሪያዎ ላይ የሚወርደውን የዝናብ ውሃ በመያዝ አጠራቅሞ ውሃውን ለአትክልት ስፍራ ማጠጫ እና ለመኪና ማጠቢያነት ይውላል። እኛ—የዲሲ መንግስት— የአንድ ጊዜ ተመላሽ **በጋሎን $2** እስከ ዝናብ በርሜል ዋጋው ድረስ እናቀርባለን (ታክስና የመጓጓዣ ወጪን አይጨምርም)። ለምሳሌ፣ 50 ጋሎን የሚይዝ የዝናብ በርሜል ካደረጉ፣ እስከ $100 የሚሆን ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ። በርሜልዎ ቢያንስ 50 ጋሎን መያዝ መቻል አለበት እንዲሁም በአንድ ንብረት ቦታ ላይ በርካታ በሜሎች ሲኖርዎ በድምሩ **እስከ $1,000** የሚሆን ተመላሽ ለእያንዳንዱ ንብረት መቀበል ይችላሉ።

ይህ ፕሮግራም RiverSmart Rebates ሲባል የቀረበውም በኢነርጂ እና አካባቢ ዲፓርትመንት ከ Alliance for the Chesapeake Bay ከሚባል ለትርፍ የማይሰራ በአካባቢው ያለ ድርጅት ጋር በመተባበር ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

በዲሲ ውስጥ የመኖሪያ ህንጻ፣ የንግድ ህንጻ ወይም የማህበረሰብ ስፍራ ካለዎት፣ ብቁ ነዎት። የሚያመለክቱበት ንብረት ዲሲ ውስጥ እስከሆነ ድረስ ለማመልከት ዲሲ ውስጥ መኖር አይጠበቅብዎትም።

## ያመልክቱ።

1. በእኛ [የዝናብ በርሜል መመሪያ] ላይ ያለውን መመሪያ በመከተል ለንብረትዎ የትኛው ምርጥ ቦታ፣ ተመራጭ የበርሜል ይዘት እንዲሁም የበርሜል አይነት መሆኑን በማወቅ ይጀምሩ። የተጠራቀመውን ውሃ እንዴት መጠቀም እንዳለብዎ፣ ከመጠን በላይ የፈሰሰውን ውሃ ወዴት መላክ እንደሚያስፈለግ እንዲሁም ለበርሜሉ እንዴት አይነት እንክብካቤ እንደሚደረግ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልግዎታል። ስለ አቀማመጥ እና የበርሜል አይነት ጥያቄዎች ካለዎት፣ በ the Alliance for the Chesapeake Bay ከሚባለው ለትርፍ የማይሰራ የአካባቢው አጋር ጋር ያለችውን Queen Richardson (qrichardson@allianceforthebay.org) ለእርዳታ ያግኟት!
2. በእኛ [የዝናብ በርሜል መመሪያ] ላይ ያለውን መስፈርት ያሟላ በርሜል ይግዙ። ለምሳሌ፣ በርሜሊ ቢያንስ 50 ጋሎን የሚይዝ እና ወደውስጡ ማየት የማይቻል (ፀሃይ ወደ ውስጡ እንዲያንጸባርቅ እንፈልግም!) መሆን አለበት። እንዲሁም መመሪያው በርካታ ቅድሚያ ተቀባይነትን ያገኙ

በርሜሎችን አካትቷል። ከዚህ ዝርዝር በርሜል እንዲገዙ አይጠበቅብዎትም ነገር ግን በርሜል መፈለጉን ሲጀምሩ ዝርዝሩ እንደሚረዳዎት ተስፋ እናደርጋለን። ለተመላሽ ማመልከቻው የገዙበትን ደረሰኝ መያዝዎን ያስታውሱ።

3. ከበርሜሉ ውጭ የአቀማመጡን ፎቶዎች ያንሱ።
4. በርሜሉን እራስዎ ያስቀምጡ ወይም ተመራጭ በርሜል የሚያስቀምጥ ሰው ይቅጠሩ። የመግጠሚያ ወጪዎች በተመላሹ ውስጥ አልተካተቱም።
5. በእኛ የዝናብ በርሜል መመሪያ መሰረት በርሜሉ ሁሉንም መስፈርቶች እንዳሟላ ለማሳየት፣ የተቀመጠውን በርሜል ፎቶዎች ያንሱ።
6. በንብረትዎ ውስጥ ላስቀመጡት ለእያንዳንዱ በርሜል የማመልከቻ ቅጽ እና የጥገና ስምምነት ይሙሉ። RiverSmart Rewards ለሚባለው በ DC Water ክፍያዎ ላይ ባለው ላይ ቅናሽ ለማመልከት፣ በማመልከቻው ጥቅል ውስጥ በአንድ አይነት ጊዜ ቅጽ አካትተናል።
7. ማመልከቻዎን፣ የጥገና ስምምነቱን፣ ደረሰኙን፣ በርሜሉ ከመቀመጡ በፊት ያሉትን ፎቶዎች እንዲሁም ከተቀመጠ በኋላ ያሉትን ፎቶዎች ለ Queen Richardson (qrichardson@allianceforthebay.org) ይላኩላት።

ለበርሜልዎ ደረሰኝ ከተቀበሉ በአንድ አመት ውስጥ ማመልከት ይችላሉ።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

### ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ፣ በሁለት ሳምንታት ውስጥ Alliance for the Chesapeake Bay ኢሜይል ያደርግልዎታል።
2. ገንዘብ ወዲያው የሚገኝ ከሆነ፣ Alliance for the Chesapeake Bay ከ 2-6 ሳምንታት ውስጥ በማመልከቻዎ ላይ ባለው አድራሻ ለተመላሽዎ ቼክ በፖስታ ይልክልዎታል። ሲያመለክቱ ገንዘብ ከሌለ፣ ገንዘብ በሚገኝበት ወቅት ተመላሽዎን ይቀበላሉ (ብዙውን ጊዜ በየአመቱ ኖቬምበር ላይ)።
3. ለበርሜሎችዎ ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋሉ። የእኛን የጥገና መመሪያ በመከተል፣ የበርሜል ማጣሪያዎችዎን ያጽዱ፣ በበጋ ወቅት ባዶ አድርገው ያቆዩት እንዲሁም የተጠራቀመውን ውሃ በመደበኛነት ይጠቀሙ። በትክክል እየሰራ እንደሆነ ለማረጋገጥ፣ በርሜልዎ መደበኛ የሆነ ትኩረት ይፈልጋል።

ተቀባይነት ካላገኙ፣ ባመለከቱ በሁለት ሳምንታት ውስጥ እርስዎን ለማሳወቅ ኢሜይል እናደርግልዎታለን። ማመልከቻዎ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ በዝርጋታዎ ላይ ምን አይነት ለውጦች ማድረግ እንደሚችሉ እናሳውቅዎታለን። ከዚያም የእርስዎን ማመልከቻ ለማጽደቅ፣ ያሉትን ለውጦች በፎቶ አድርገው ሊልኩልን ያስፈልጋል።

### ሁሉም ብቁ አመልካቾች ተመላሹን ያገኛሉ?

አዎ። በእኛ የዝናብ በርሜል መመሪያ ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የእርስዎ የዝናብ በርሜል እስካሟላ ድረስ፣ ተመላሽ ያገኛሉ።

**ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?**
ከስር ባሉት የተለዩ ሁኔታዎች፣ በርሜሉ ሁሉንም መስፈርት እንዳሟላ ለማረጋገጥ፣ በርሜሉን ከማስቀመጥዎ በፊት እኛን ማግኘት አለብዎት።

- የራስዎን በሜል የሚገነቡ ከሆነ፣ ከመጀመርዎ በፊት የንድፍ ስኬቹን እና የመገጣጠሚያዎቹን ደረሰኞች ለ Queen Richardson (qrichardson@allianceforthebay.org) ኢሜይል ያድርጉ። ለተመላሹ የእርስዎ በርሜል መስፈርቶቹን በሙሉ እንዳሟሉ እናረጋግጥልዎታለን።
- የዝናብ ውሃ cistern መትከል ከፈለጉ፣ ከመግዛትዎ በፊት ለመግዛት ያቀዱትን የ cistern ዝርዝሮች ለ Queen Richardson (qrichardson@allianceforthebay.org) ኢሜይል ያድርጉ። Cisterns ከመደበኛ በርሜሎች ተለቅ ያሉ ናቸው እንዲሁም በርሜሎች ሁልጊዜ ማለት ይቻላል ከመሬት በላይ ሲቀመጡ cistern ከመሬት በላይ ወይም በታች ሊደረጉ ይችላል። ለተመላሽ የእርስዎ cistern መስፈርቶቹን ማሟላታቸውን እኛ እናረጋግጣለን።

**ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?**
መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች ቦታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎን Queen Richardson በ Alliance for the Chesapeake Bay ላይ በስልክ ቁጥር (202) 910-9796 ያነጋግሯት። ወይም በ qrichardson@allianceforthebay.org ላይ በርዕሰ መስመር ""Rain Barrel Rebate Question" ብለው ኢሜይል መላክ ይችላሉ። ለተመላሽ መስፈርቱን ማሟላትዎን እንድናረጋግጥልዎ ከፈለጉ፣ ከመቀመጡ በፊት እና በኋላ ያሉ ፎቶዎችን እንዲሁም የበርሜሉ ደረሰኝን ያካትቱ።

ስለፕሮግራሙ በዲሲ መንግስት ውስጥ ያለን አንድ ሰው ለማነጋገር ከፈለጉ፣ የእኛን RiverSmart Homes ቡድንን በ (202) 535-2252 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ፣ ከ 9 am እስከ 5 pm ባለው ሰአት ውስጥ ማግኘት ይችላሉ ወይም ወደ እኛ በ riversmarthomes@dc.gov በርዕሰ መስመር "Rain Barrel Rebate Question" ብለው ኢሜይል መላክ ይችላሉ።

**ቤቴን የበለጠ ለአካባቢ ተስማሚ ለማድረግ አሁንም ቢሆን እርዳታ ያስፈልገኛል። ምን ማድረግ አለብኝ?**
ቤትዎን ይበልጥ ለአካባቢ ተስማሚ የሚያደርጉ እርስዎን ሊረዱ የሚችሉ ሌሎች መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**

**በርሜል የት መግዛት ይኖርብኛል?**
በእኛ የዝናብ በርሜል ዝርዝር ውስጥ የተዘረዘሩት ቅድሚያ ተቀባይነትን ያገኙ ብዙዎቹ በርሜሎች ኦንላይን ላይ ይገኛሉ። እንዲሁም በርካታ የአካባቢ ሃርድዌር ማከማቻዎች የዝናብ በርሜሎችን ይዘዋል ወይም በጥቂት ቀናት ውስጥ በልዩ ሁኔታ አዝዘው ማስመጣት ይችላሉ። Annie's Ace Hardware በ

Petworth (202-726-2658) እና Brookland (202-529-2658) ያሉ ቅድሚያ ተቀባይነትን ያገኙ በርሜሎችን፣ የማከፋፈያ መሳሪያዎችን እንዲሁም ሌሎችን ያቀርባሉ።

## የራሴን በርሜል ሳስቀምጥ ወይም የጥላ ዛፍ ወይም የዝናብ በርሜልን የመሳሰሉ ሌሎች የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ሳዘጋጅ እርዳታ ላገኝ እችላለሁ?

ምን አልባት! የእኛ RiverSmart Homes ፕሮግራም ዝቅተኛ ዋጋዎች እና ለዝናብ በርሜሎች፣ ዛፎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች እንዲሁም ቤይስኬፒንግ የማዘጋጀት እርዳታዎችን ያቀርባል። ነጠላ የቤተሰብ ቤት (ወይም አራት ወይም ከዛ በታች ክፍሎች ያሉት ህንጻ) ካለዎት፣ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በበርሜሉ አይነት ላይ ተመስርቶ በአንድ የዝናብ በርሜል ከ $50-70 ይከፍላሉ እና ለማስቀመጥ እና ቀሪዎቹን ወጪዎች እንሸፍናለን። RiverSmart Homes ውስን የሆኑ የበርሜል አይነቶችን ብቻ ሲያቀርብ በእያንዳንዱ ንብረት ላይ ሁለት በርሜሎችን ብቻ ይሸፍናል።

RiverSmart Rebates የመኖሪያ፣ የንግድ እንዲሁም የማህበረሰብ ስፍራን አጠቃልሎ ለማንኛውም የንብረት ባለቤት ክፍት ነው። የሚከተለውን ከመረጡ፣ የተመላሽ ፕሮግራም ከ RiverSmart Homes ይልቅ የተሻለ የሚመጥን ሊሆን ይችላል፡

- በእኛ የዝናብ በርሜል መመሪያ መስፈርቶች የሚያሟሉትን ማንኛውንም በርሜል ይምረጡ ወይም የራስዎትን ይስሩ።
- ስራውን ለሚያከናውነው ባለሙያው ለመመደብ ረጅም የወረፋ ጊዜያትን ያስቀሩ
- ስራዎቹን ለሚያከናውን ሰው ይምረጡ ወይም እራስዎ ስራውን ያከናውኑ

## የጥላ ዛፍ እና የዝናብ በርሜልን የመሳሰሉ ሌሎች የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ተመላሽ ለማግኘት እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

በራስዎ ወይም እርስዎ በመረጡት የሚያከናውን ባለሙያ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶችን ሲገነቡ፣ ከእኛ - የዲሲ መንግስት ተመላሽ መቀበል ይችላሉ። የብቁነት መስፈርት፣ የማመልከቻ ሂደት፣ እንዲሁም የተመላሽ መጠን በፕሮጀክቱ አይነት ላይ በመመስረት ይለያያል እንዲሁም ከመገንባትዎ በፊት መተግበር ሊኖርብዎት ይችላል። ተመላሽ ስለምንሰጥባቸው የሚከተሉት ፕሮጀክቶች የበለጠ መማር ይችላሉ፡

- የዝናብ ውሃን ለመያዝ የሚያስችሉ ተክሎችን እድገት ለመርዳት የሚሆኑ **አረንጓዴ ጣሪያዎች**
- ከተለመደው አስፋልትና የኮንክሪት ገጽታ ይልቅ የዝናብ ውሃን ለመያዝና በጊዜያዊነት ለማቆየት የሚያስችሉ **አስተላላፊ ገጽታዎች**
- **የዝናብ አትክልት ስፍራዎች** ወይም ከዝናብ ውሃ ውስጥ ያለውን ብክለት ለማጣራት፣ ኢንጂነርድ የሆነ ሌላ የአትክልት ስፍራ ሲስተም
- በአፈር ውስጥ የዝናብ ውሃ ማቆየትን ለመርዳት **የጥላ ዛፎች**

## የዝናብ በርሜል በማድረጌ ሌላ የገንዘብ እርዳታ ላገኝ እችላለሁ?

አዎ! ለዚህ ፕሮግራም ሲያመለክቱ፣ በ DC Water ክፍያዎ ላይ **RiverSmart Rewards** ለሚባለው ቅናሽ ማመልከት እንዲችሉ እንረዳዎታለን። ይህ ቅናሽ እንደ ዝናብ በርሜሎች ያሉ የበቁ አረንጓዴ

ፕሮጀክቶችን በመጠቀም የውሃ ፍሰትን በንብረታቸው ላይ እንዳይሆን ለሚከላከሉ የንብረት ባለቤቶች ነው።

**እነዚህ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች የዲሲ ከተማን እንዴት ሊረዱት ይችላሉ?**
እንደ የዝናብ በርሜሎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች እንዲሁም የጥላ ዛፎችን የመሳሰሉ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች ንብረትዎን የሚያጥለቀልቀውን እና ወደ ወንዞች የሚፈስሰውን የተበከለ የዝናብ ውሃ መጠን እንዲቀንስ ይረዳሉ። ይህ የ Anacostia ወንዝን፣ Potomac ወንዝን እንዲሁም Rock Creek ከአደገኛ ብክለቶች እንድንጠብቅ ይረዳናል።

**ተቀባይነት ሳላገኝ ብቀር ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?**
አዎ። በሁኔታዎ ላይ ያለው ለውጥ ብቁ ያደርገኛል ብለው ካመኑ፣ እንደገና ለተመላሽ ማመልከት ይችላሉ።

ተቀባይነት አግኝተው ነገር ግን ባመለከቱበት ወቅት ገንዘብ ከሌለ፣ ዳግም ማመልከት አያስፈልግዎትም። ገንዘብ ሲገኝ (ብዙውን ጊዜ በየአመቱ ኖቬምበር ላይ ነው) የእርስዎን ተመላሽ በፖስታ እንልክልዎታለን።

**የተጠራቀመውን ውሃ ወደምጠቀምበት ስፍራ ለመላክ ተጨማሪ የውሃ ግፊት እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**
የተጠራቀመውን ውሃ መጠቀም ወደሚፈልጉበት የትኛውም ስፍራ ለመላክ ተጨማሪ የውሃ ግፊት ያስፈልግዎታል። የውሃ ግፊቱን ለመጨመር፣ በርሜልዎ ላይ ከፓምፕ ጋር ማገናኘት ይችላሉ። ከግምት ውስጥ ሊያስገቧቸው የሚችሉ የፓምፖች ምሳሌ ከሚባሉት ውስጥ በሶላር ሃይል የሚሰሩ ፓምፖች በ Aquabarrel፣Algreen ወይም Home Depot ላይ ሊያገኟቸው ይችላሉ።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*